ሠ/ ፓርላሜንታዊ ያለመከሰስ መብት

አስከፊ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በቀር የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤት አባላትን ከመያዝ ወይም ከመከሰስ ይከልላቸዋል።

ሁለት ታዋቂ የሆኑ ምሁራን እና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ብርሃኑ ነጋ እና መስፍን ወልደ ማርያም ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን በ 1993 ዓ.ም. ለረብሻ አነሳስታችኋል ተብለው ከተከሰሱ በኋላ የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሐምሌ 1997 ዓ.ም. በፍርድ ቤቱ ለሚታየው ክስ መከላከያቸውን አዘጋጅተው እንዲቀርቡ አዝዟል።

በዓመቱ መጨረሻ ከዚህ የሚከተሉት ታጋቾች እንደታሠሩ ነበሩ ፦ አልአዛር ደሴ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአማካሪነት ሲሠራ የነበረ የአሜሪካ ዜጋ፣ የተያዘ እና በሥልጣን ያላግባብ በመጠቀም የተከሰሰ (በዋስ መፈታታ የማይፈቀድለት ጥፋት) በ1993 ዓ.ም. ከ3 ዓመት በላይ ክሱ በፍትህ አደባባይ እንዲታይለት እየጠበቀ ነው። 24 ነጋዴዎች እና የመንግሥት ሹማምንት ሙስና ፈጽመዋል በመባል ተይዘው በይፋ ክስ ያልተመሰረተባቸው። በ1993 ዓ.ም. የተያዘው የኤርትራ ኤምባሲ (ኦፊሻል)፣ ሹፌር ያለበትም የማይታወቀው።

በሺህዎች የሚቆጠሩ የወንጀል ተጠርጣሪዎች አንዳንዶቹ ለጥቂት ዓመታት ፣ ክስ ሳይመሰረትባቸው ታግተው እንደሚገኙ ተዘግቧል። ከታጋቾቹ ውስጥ አንዳንዶቹ ከኦነግ እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተወነጀሉ የኦሮሚያ የተማሪዎች ነውጥ ከፈነዳ በኋላ የተያዙ ናቸው።

መንግሥት ክስ ሳይመሰርትባቸው በርካታ ሰዎችን፣ አንዳንዶቹን ለዓመታት፣ ፖሊስ ምርመራውን እስከሚጨርስ በጎንደር ወህኒ ቤት አግቶ ይገኛል። ሙጭ በሪሁን ሰው በመግደል ተከስሶ እሱ ገድሎታል የተባለው ሰውዬ የተገደለው ሙጭ ከታገተ በኋላ ቢሆንም፣ ለ3 ዓመታት ከስድስት ወር ብቻውን በመገለል ታስሯል። በ1994 ጉዳዩን ማየት ተጀምሮ ነበር። ሆኖም ፍርድ ቤቱ ከችሎት የተነሳ በመሆኑ እስካለፈው ታህሣሥ ድረስ የጉዳዩ መታየት ከምን እንደደረሰ አልታወቀም። እስከዚያን ጊዜ ድረስ እሱ እንደታገተ ቆይቷል። ወንድአንተ መስፍን ከ 1996 ዓ.ም ጀምሮ በነፋስ መውጫ እስር ቤት በደቡብ ጎንደር ታግቶ የሚገኝ ሲሆን፣ ምንጊዜም ፍርድ ቤት

ቀርቦ ክስ በአግባቡ አልተመሰረተበትም። በመኢአድ ዘገባዎች መሰረት በዓመቱ ውስጥ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ታጋች ሁኔታ በተመለከተ ምንም ለውጥ አልነበረም።

ረ/ ፍትሃዊ የሆነ ይፋ የፍርድ ሂደትን መንፈግ

ሕገ መንግሥቱ ነፃ የሆነ የፍትሕ ሥርዓት እንዲኖር ደንግጓል። ሆኖም ግን የፍትሕ ሥርዓቱ ደካማ እንደሆነ እና የሥራ ጫና እንደበዛበት ቆይቷል። የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የፍትሕ ነፃነትን በሚያሳዩ ምልክቶች መሥራታቸውን ቢቀጥሉም ፣ በግብር ግን በብዙ ክልሎች ከባድ የሆነ በአግባቡ የሰለጠነ ሠራተኛ እጥረት እንደዚሁም የፋይናንስ ችግሮች አሉ። እነዚህ ተነባብረው ዜጎች በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉላቸውን ጥበቃዎች ሙሉ በሙሉ ማግኘት አልቻሉም።

መንግሥት የፍትሕ ሥርዓቱን ከማዕከላዊነት የማላቀቁንና በፌዴራላዊ መስመር በማወቀር ፍርድ ቤቶችን በወረዳ፣ በአካባቢ ፣ እና በክልል ደረጃ ማቋቋሙን ቀጥሏል። የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ሕግን፣ ክልል ዘለል ጉዳዮችን፣ እና ብሔራዊ ፀጥታን/ደህንነትን የሚመለከቱ የሥር እና የይግባኝ ጉዳዮችን እያዩ ብይን ሰጥተዋል። የክልል የፍትሕ ሥርዓቱ፣ የፌደራል የፍትሕ ሥርዓቱን በማንፀባረቅ፣ የወረዳ፣ የአካባቢ፣ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ያሉት ሆኖ በይበልጥ እራስ ገዝ (ኦቶኖመስ) ነበር። በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ሦስት ዳኞች የሚቀመጡባቸው ሁለት ችሎቶች የወንጀል ጉዳዮችን ይመለከታሉ/ይዳኛሉ። ከ1994 ዓ.ም. በፊት በሚገባ የተደራጁ የክልል ፍርድ ቤቶች ባለመኖራቸው የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልል ጉዳዮችን ይሰሙ ነበር። ከ1994 ዓ.ም. ወዲህ የክልል ፍርድ ቤቶች በመጠናከራቸው የክልል ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ በሥፍራው ነው የሚሰሙት /የሚታዩት።

የፌደራል የፍትሕ ሚኒስቴር የክልል ጽ/ቤቶች በሥፍራው የፍትሕ ሁኔታን ይከታተላሉ። አንዳንድ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል ፍርድ ቤቶች በክልሎች ሥራቸውን ባለመጀመራቸው፣ የሥፍራውን እና የፌደራል ጉዳዮችን ይዳኛሉ። በአጠቃላይ የፌደራል የፍትሕ ሥርዓቱ በክልሎች መኖር ውሱን ነበር። በአንዳንድ ሥፍራዎች የደረሱ ሁኔታዎች እንዳስረዱት አንዳንድ የአካባቢ ሹማምንት ለበላይ ባለሥልጣን ኃላፊነት እንደሌላቸው ያምናሉ። የክልል ሕግ አውጭ አካላት ክልሉን

የሚመለከቱ ሕግጋት እስከሚወጡ ድረስ፣ ሁሉም ዳኞች የሚመሩት በፌደራል የሥነ ሥርዓት ሕግ እና በሌሎቹ መሠረታዊ ሕጎች ነው።

በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ተመክሮ ያለው ሠራተኛ እጅጉን ያለመኖሩን ችግር ለመበቀል ፣ መንግሥት የበታች ፍርድ ቤት ዳኞችን እና ዓቃቢያነ ሕግን ለይቶ በማውጣት ማሰልጠኑን ቀጥሏል። ያም ቢሆን የክፍያው መጠን የሚፈለገውን ያህል ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን እንደማይስብ ሹማምንቱ ይናገራሉ።

በሕገ መንግሥቱ መሰረት የተከሰሱ ሰዎች በመደበኛ ፍርድ ቤት በግልጽ ችሎት ክስ ከተመሰረተባቸው በኋላ "ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ" የመዳኘት እና እራሳቸው በመረጡት የሕግ አማካሪ /ጠበቃ የመወከል መብት አላቸው ። ሆኖም በግብር መዳኘት ከመጀመሩ በፊት ለረጅም ጊዜ መታገት የተለመደ ነበር። ዝግ ችሎቶች ተደርገዋል፤ አንዳንድ ጊዜም ታጋቾች ከጠበቃቸው ጋር ግንኙነት ማድረግ ምንም ያህል አልተፈቀደላቸውም፣ ወይም ከነጭራሹ ግንኙነት ማድረግ አልተፈቀደላቸውም። (ክፍል1 መን ይመልከቱ)። ሕገ መንግሥቱ አንድ ሰው (ጥፋተኛነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ) ንፁህ ሆኖ እንዲቆጠር ቢደነግግም፣ በግብር ተከሳሾች ለዚህ ጥበቃ አልታደሉም። የአገሩ ተወላጅ ለሆኑ ተከሳሾች የሕዝብ ተከላካይ ጽ/ቤት በተለይ ልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት በሚያቀርበው ክስ ረገድ የሥራው መስክ እጅግ ውስን ቢሆንም ፣ ጠበቃ ያቆማል። የክሱ መታየት ከመጀመሩ በፊት የተከሳሽ ጠበቃ የዐ ቃቤ ሕግን ማስረጃ ማግኘትን በግልጽ የሚከለክል ሕግ ባይኖርም፣ እና ይልቁንም ሕጉ በሙስና የተከሰሱ ሰዎች የክሱ መታየት ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚቀርቡባቸውን ማስረጃዎች እንዲያዩ መደረግ እንዳለበት ሕጉ በግልጽ ቢደነግግም ፣ ይህ ተዘውትሮ ተነፍጓል።

ሕገ መንግሥቱ አስቀድሞ ለተቋቋሙ የሃይማኖት እና ልማዳዊ ፍርድ ቤቶች ሕጋዊ እውቅና ሰጥቶ የፌደራልና የክልል ሕግ አውጭዎች እነዚህን ፍርድ ቤቶች እንዲያውቋቸው ሥልጣን በመስጠት ደንግጓል። በሕጉ መሰረት ልማዳዊ ወይም የሃይማኖት ፍርድ ቤት አንድን ጉዳይ ማየት ከመጀመሩ አስቀድሞ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች መስማማት አለባቸው። የሸሪአ (እስላማዊ) ፍርድ ቤቶች ሙስሊሞችን በተመለከተ የሃይማኖት እና የቤተሰብ ጉዳዮችን ማየት ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ሌሎች ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች፣ የሽምግልና ጉባኤን የመሳሰሉት ተግባራቸውን ቀጥለዋል። እነዚህ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በሕግ ባይፀኑም፣ በገጠር አካባቢ ለሚኖሩ

እና በአጠቃላይ መደበኛ የፍትሕ ሥርዓቶች ምንም ያህል ለማይደርሳቸው አብላጫ ዜጎች ችግሮቻቸውን ፈትተውላቸዋል።

በጥቅምት 18/97 ዓ.ም. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሰባተኛ የወንጀል ቅርንጫፍ ሥራውን ጀምሯል። ይህ ፍርድ ቤት የተቋቋመው በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚደርሱት የወሲብ ጥቃት ጉዳዮች እንዲያስታናግድ ነበር። ጉዳዩ በሚታይበት /በሚሰማበት ጊዜ ተደፋሪዎች ከተከሳሽ በአካል እንዲለያዩ ተደርጎ ፣ የምስክርነት ቃላቸውንም የሚሰጡት ለውጭ ዝግ ሆኖ በተወሰነ ክልል ብቻ በሚታይ የቴሌቪዥን ስርጭት አማካይነት ነበር። በዓመቱ መጨረሻ ፍርድ ቤቱ በወሲብ ጥቃት ጉዳዮች ላይ ስድስት የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቶ ከ4 እስከ 20 ዓመታት የሚደርሱ የእስራት ቅጣቶች ወስኗል።

ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች የሚፈጸሙ ጥፋቶችን ሁሉ ለመስማት ሦስት ፌደራል ዳኞች በአንድ ችሎት ላይ ተቀምጠዋል። ወጣት አጥፊዎችን የሚመለከቱ በብዛት የተወዘፉ ጉዳዮች ነበሩ፣ ተከሳሽ ልጆችም ጉዳያቸው እስከሚሰማ ድረስ ከጎልማሶች ጋር ታግተው መቆየት ነበረባቸው።

በ1990 ዓ.ም. ከኤርትራ ጋር ጦርነት መከፈቱ የወታደራዊ ፍትሕ ሥርዓቱን ጎድቷል። የሠራዊቱ ባፋጣኝ መስፋፋት የሰለጠኑ ወታደራዊ የሕግ አዋቂዎችን እና ዳኞችን አስፈላጊነት በጣም ከፍ ባደረገበት ጊዜ መኮንኖችን እና ባለሌላ ማዕረጎችን ለማሰልጠን ይሰጥ የነበረው የውጭ ዕርዳታ አብዛኛው ተቋረጠ።

በመንግሥቱ ኃይለማርያም መንግሥት ጊዜ (1967-83 የደርግ አገዛዝ በመባልም ይታወቃል) ስለ ተፈጸሙት የመብት እረገጣዎች አንድ የታሪክ ምዝገባ እንዲያዘጋጅ እና ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በወንጀለኛነት ኃላፊ የነበሩትን ለፍርድ እንዲያቀርብ በ1984 ዓ.ም. ስለተቋቋመው የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት አዲስ መረጃ አልነበረም። በደርግ ዘመን ከተፈጸሙት ጥፋቶች ጋር በተያየዘ 1,000 ያህል የሚሆኑ ሰዎች እንደታገቱ ነበሩ። ፍርድ ቤት የመደባቸው ጠበቆች ፣ አንዳንድ ጊዜ ካለበቂ ክህሎቶች እና ተመክሮዎች ብዙዎቹን ተከሳሾች ወክለዋል።

መንግሥት 100 ያህል የፖለቲካ እስረኞችን ስለማገቱ ዘገባዎች ነበሩ፣ መንግስትም ቀመዓአኮ በቋሚነት በተወሰነ ጊዜ እነዚህኑ እንዲገናኝ ፈቅዷል።

ቀ/ በግል መብት፣ በቤተሰብ ፣ በቤት ወይም በመፃፃፍ ላይ ከሕግ ውጭ ጣልቃ መግባት

የግል ንብረትን ለመበርበር፣ የፍርድ ቤት የብርበራ ትዕዛዝ እንዲኖር ሕጉ ይጠይቃል። ሆኖም በግብር፣ በተለይ ከአዲስ አበባ ውጭ ፣ ብዙውን ጊዜ ፖሊስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያገኝ የሰዎችን ንብረት ይበረብራል። (ክፍል 1 መን ይመልከቱ) ፖሊስ ወደ ግለሰቦች ቤት ገብቶ፣ አታልሎ ገንዘብ መውሰድን ጨምሮ የወንጀል ሥራዎችን ለመፈጸም አንዳንድ ጊዜ ተጭበርብሮ የተሠራ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንደሚጠቀም የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች ተናግረዋል። በዓመቱ ውስጥ የፌደራል ፖሊስ አባላት የውሸት የፍርድ ቤት ትእዛዝ በመጠቀም ጭምር ሰዎችን ስለመዝረፋቸው ዘገባዎች ነበሩ።

ፖሊሶች ሰላማዊ ሰዎች ቤት በግድ ስለመግባታቸው ዘገባዎች ቀጥለዋል። እንደዚሁም የፀጥታ ኃይሎች ካለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰዎችን በውድቅት ሌሊት ከቤታች ስለመውሰዳቸው ዘገባዎች ነበሩ። ለምሳሌ በሚያዝያ ወር በአምቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የእጅ ቦምቦች አፈንድተዋል የተባሉ ኦሮሞ ተማሪዎች በእኩለ ሌሊት ከየመኖሪያቸው ተለቅመው መወሰዳቸው ተዘግቧል።

የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ቤቶቻቸው እንደተቃጠሉባቸው እና የጽሕፈት ቤቶቻቸውም እንደተዘረፉባቸው ዘግበዋል። (ክፍል 3ን ይመልከቱ)

መንግስት ከሕግ ውጭ እንደ ኢንተርኔት መገናኛዎች ያሉትን የግል ግንኙነቶችን ይከታተላል/ ይሰልላል። የኤሌክትሮኒክ መገናኛዎች በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ ነበሩ። የተለዩ ግለሰቦች ስለሚያደርጉት እንዲከታተሉ እና እንዲዘግቡለት መንግሥት ገንዘብ በሚከፈላቸው የመረጃ አቀባዮች ሥርዓት ተጠቅሟል።

በገጠር አከባቢዎች ቤተሰቦችን አስገድዶ ማፈናቀል አንደነበረ በዓመቱ ውስጥ ዘገባዎች ነበሩ። መንግሥት በበኩሉ ቤተሰቦችን በድርቅ ከሚጠቁ አካባቢዎች ወደ ለም መሬቶች በመዛወር የተከናወነው፣ የሰፈራ ፕሮግራም በሙሉ ፈቃደኝነት

እንደሆነ ተናግሯል። ነገር ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ያሉት የሥፍራው ባለሥልጣናት የሰፈራ ተራዎችን በመበወዝ የተቃዋሚ ደጋፊዎችን ወደ ሰፈራ በማስቀደም ላይ አነጣጥረዋል በማለት ይከሳሉ። እንደ ድንበር የለሽ ሐኪሞች ያሉት መያዶች ፣ አንዳንድ ጊዜ መንግሥት ምንም መሰረተ ልማት ወይም የንፁህ ውሃ አቅርቦት ወደሌለበት አካባቢ ሰዎችን እየወሰደ በማስፈሩ፣ ባልተለመደ ሁኔታ ቁጥሩ ከፍ ያለ የሕፃናት መሞትን እንዳስከተለ ዘግበዋል።

ቀደም ካሉት ዓመታት በሚለይ ሁኔታ ፣ መንግሥት አዲስ አበባን ለ «ማፅዳት» በሚያደርገው ሙከራ ነዋሪዎቹን ከነበሩበት በግድ ወስዶ ከከተማ ውጭ ባሉ አከባቢዎች ስለማስፈሩ ዘገባዎች አልነበሩም።

በአንዳንድ የደቡብ ክልልና የኦሮሚያ ክልል፣ የአማራ ክልል የገጠር አካባቢዎች የሥፍራው ባለሥልጣናት ፣ ለገጢው ቡድን ድጋፍ ለማጠናከር በማሰብ፣ እንደገና የመሬትን መከፋፈል፣ የምግብ እርዳታንና ማዳበሪያ ማቅረብ ማቆምን በማስፈራሪያነት እንደሚጠቀሙባቸው ከኢስመትቤ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚታመኑ ዘገባዎች መቅረብ ቀጥሎ ነበር። ግለሰቦች የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባል እንዳይሆኑ ወይም ንብረት እንደያከራዩዋቸው በመከልከል ላይ ያነጣጠረ የገገርው ፓርቲ ወይም የመንግስት ማዋከብ እንደነበረ በርካታ ዘገባዎች ቀርበዋል። ከባድ ማዋከብ እና በኃይል መጠቀም፣ ድበደባዎች፣ ቤት ማቃጠል እና ግድያ ጭምር በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ ሲካሄድ አንደነበር አያሌ ዘገባዎች ገልዘጸዋል (ክፍሎች 1ሐ፣ 1መን ፣ እና 3ን ይመለክቱ)።

እንደዚሁም መምህራን እና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባል ከሆኑ የሥራ ቅጥራቸው ያከትም እንደነበረ የታመኑ ዘገባዎች ነበሩ።

የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት (ዲኢሕዴሕ) በገለጸው መሠረት የክልሉ መንግሥት አባላቱን፣ በተለይም መምህራንን፣ ከሥራቸው ማሰናበት እንደቀጠለ ነበር። ለዚህ ምላሽ በመስጠት የክልሉ መንግሥት በበኩሉ የመንግሥት ሠራተኞች የመንግሥትን ፖሊሲ መተግበር አለባቸው ብሏል። ክልሉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የሆኑትን ሠራተኞች የመንግሥት ፖሊሲን አይፈጽሙም በማለት ይከሳቸዋል።

የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ማንም ባለትዳር ፍቺ ከተፈጸመ ወይም ከተጋቢዎች አንዳቸው ከሞቱ በኋላ እንደገና ማግባት የሚፈልግ ለ6 ወራት እንዲቆይ ያስገድዳል (ክፍል 5ን ይመልከቱ)። አንድ ሴት የቀድሞ ባለቤቷን ፅንስ ቋጥራ እንደሆነ ለመወሰን ይህ የመቆያ ጊዜ አስፈላጊ መሆኑን መንግስት ጸንቶበት ነበር።

ለጥያቄ የሚፈለጉ፣ እንደ ኦነግ ተጠርጣሪ አባላት ያሉት፣ ሰዎች ቤተሰብ አባላት መንግሥት ሲያግት ነበር።

ክፍል 2 የሚከተሉትን ጨምሮ የሲቭክ ነፃነቶችን ማክበር

ሀ/ የመናገር እና የፕሬስ ነፃነት

ሕገ መንግሥቱ የመናገር እና የፕሬስ ነፃነትን ደንግጓል። ሆኖም ፣ መንግስት እነዚህን መብቶች በግብር አጣብቧል። መንግሥት ያልሆነ የፈጠራ መረጃ አትማችኋል፣ እንደዚሁም የፕሬስ ሕግን በሌላ አኳያ ጥሳችኋል በማለት ጋዜጠኞችንና አርታኢዎችን ለፍርድ ማቅረቡን እንደቀጠለበት ነበር። መንግሥት የዜና ማሰራጫዎችን በሙሉ እንደተቆጣጠረ ነበር። የግል እና የመንግሥት ጋዜጠኞች ራስን በራስ ሳንሱር ማድረግ አዘውትረው ተጠቅመዋል። ያም ሆኖ የግሉ ፕሬስ ንቁ እንደሆነና ፣ መንግስትንም አጥብቀው የሚተቹ ጽሁፎች አዘውትሮ ማተሙን እንደቀጠለ ነበር።

ነፃ የኅትመት ሚዲያዎች ንቁ ሆነው በሰፊው የተለያዩ አስተያየቶችን ይገልጹ ነበር። ይህንንም ሲያደርጉ የነበረው ሕግ አውጭ ፣ አስፈፃሚ እና ተርጓሚ የሆኑትን የመንግሥት ቅርንጫፎች የመቅረብ ዕድላቸው እንደተጣበበ ሳለ እና በመንግስት የማስፈራራትና የማዋከብ ተግባራት እንደተጋለጡ ነበር።

ባለሥልጣናት የሕግ እርምጃ እንደሚወሰድበት አዘውትረው ቢያስፈራሩትም፣ የግሉ ፕሬስ መንግሥትን የሚተቹ ጽሑፎችን ማተሙን እና የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችን መዝገቡን እንደቀጠለ ነበር። ብዙው የግል ፕሬስ በአዘጋገብ ሙያዊነት ቢጎድለውም፣ አንዳንድ የኅትመት ሚዲያዎች በይበልጥ ኃላፊነት ወደሰፈነባቸው ሥራዎች መሸጋገር ቀጥለዋል። በርካታ ኅትመቶች ከተለያዩ የጎሳ ቡድኖች ፣ በተለይም ከአማሮች እና ከኦሮዎች ጋር የተሳሰሩ ሆነው፣ መንግሥቱን በጎሰኝነቱ አምርረው ተችተውታል።

መንግሥት የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን የስርጭት ሚዲያ በሙሉ መቆጣጠሩን ቀጥሏል። ሕጉ የግል ሬዲዮ ጣቢያዎችን የሚፈቅድ ቢሆንም፣ የቁጥጥር ማስፈጸሚያው አልነበረም፤ ነፃ የሬዲዮ ጣቢያዎችም አልነበሩም። መንግሥት በሚያንቀሳቅሰው የኢትዮጵያ ሬዲዮ የስርጭት ሰዓት ለግል ቡድኖች እና ግለሰቦች ለፕሮግራሞች እና የንግድ ማስተዋወቂያ መግዛት ለሚፈልጉ ሲሸጥ ነበር። መንግሥት ብቸኛውን የቴሊቪዥን ጣቢያ ሲያንቀሳቅስ እና የዜና ስርጭቶችንም በጥብቅ ሲቆጣጠር ነበር። በዓመቱ መጨረሻ ምንም ማመልከቻዎች ያልቀረቡ ቢሆንም ለሁለት አዲስ ኤፍ ኤም የግል ጣቢያዎች ፍላጎት ያላቸው ማመልከቻ እንዲያቀርቡ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኤጀንሲ በመስከረም 1996 ዓ.ም. ጋብዞ ነበር ። የፖለቲካ እና የሃይማኖት ድርጅቶች የስርጭት ጣቢያ ባለቤቶች እንዳይሆኑ የብሮድካስቲንግ ሕግ ይከለክላል። የውጭ ዜጋ ባለቤትነትም ክልክል ነው።

ዓለም አቀፋዊ የዜና ስርጭቶችን ማግኘት አልተከለከለም ነበር። ሳተላይት መቀበያ የግል ሳህኖች እና ፋሲማይል ማሽኖችን እና ሞዴሞችን ከውጭ ማስገባት ተፈቅዷል። ሆኖም ፣ ይህን ቴክኖሎጂ ማግኘት በዋጋው ከፍተኛነት እና በብቸኛው የአገልግሎት ሰጪው ባለቤት በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን አቅም ውሱንነት ምክንያት አገለግሎቱን ማግኘት የማይከጀል ነበር።

የውጭ ጋዜጠኞች ሥራቸውን በተሻለ ነጻነት ማከናወን በመቀጠል፣ ብዙ ጊዜም የመንግስት ፖሊሲዎችን የሚነቅፉ/የሚተቹ ጽሑፎችን ጽፈዋል። እነሱ ወይም የአገሬው ተባባሪያቸው ከአገሬው ነፃ ጋዜጠኛ በበለጠ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ለማግኘት እድሉ ነበራቸው። ብዙ የውጭ የዜና ድርጅቶች የአዲስ አበባ ጽሕፈት ቤቶቻቸው ሠራተኞች ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ ሆነው የሚሠሩ የአገሬው ጋዜጠኞች ነበሩ።

በዓመቱ ውስጥ ፖሊስ ጋዜጠኞችን ስለማዋከቡ፣ መደብደቡ ፣ እና ማገቱ ዘገባዎች ነበሩ ። ለምሳሌ በመጋቢት 20/96 የታጠቀ ፖሊስ የጦቢያ ጋዜጣ እና መጽሔት ምክትል ዋና አዘጋጅ የሆነውን አጥናፉ ዓለማየሁን ፣ ካራ ቆሬ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ነዋሪዎቹ ቤቶቻቸውን ስላፈረሱባቸው የሚያሰሙትን ሮሮ በተመለከተ ቃለ መጠይቅ ሲካሄድ ፣ ደብድቦታል። አጥናፉ ለ1 ቀን ታግቶ ዓለም ገና ፖሊስ ጣቢያ